# የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ስብሰባ፡ የቤተሰብ/አሳዳጊ አጠቃላይ እይታ

የተማሪ ስም፦ ቀን፦

***IEP (የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም) ምንድነው?***

የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ለልጅዎ ብቻ የተነደፈ እቅድ ነው። ዓመታዊ ግቦችን በመጥቀስ እና የልጅዎ ጠንካራ ጎኖች እና ትምህርታዊ ፍላጎቶችን በመለየት ልጅዎ ለመማር እና ትምህርት ላይ አስፈላጊውን እድገት ለማሳየት የሚያስፈልጉዋቸውን ድጋፎች እና አገልግሎቶችን ይዘረዝራል።

**በ*IEP* ቡድን ውስጥ ያለው ማነው?**

- እርስዎ (ወላጁ ወይም አሳዳጊው)*
- የትምህርት ቤት አስተዳዳሪ (እንደ ርእሰ መምህር ወይም ረዳት ርእሰመምህር ያሉ - ብዙ ጊዜ የአከባቢ ትምህርት ኤጀንሲ ተወካይ (LEA) በመባል ይታወቃሉ)*
- የአጠቃላይ ትምህርት መምህር (እንደ የልጅዎ ክፍል መምህር)*
- የልዩ ትምህርት መምህር *
- ማንኛውም የተዛማጅ አገልግሎት ሰጪዎች (እንደ የንግግር ቴራፒስት ወይም የኦኪፔሽናል ቴራፒስት)
- ልጅዎ (ዕድሜያቸው ከ14+ በላይ የሆኑ ልጆች እንዲሳተፉ ተጋብዘዋል፣ ነገር ግን ትንንሽ ልጆች እንደአግባቡ መሳተፍ ይችላሉ)
- በእርስዎ ወይም በትምህርት ቤቱ የተጋበዘ ሌላ ማንኛውም ሰው
  ማስታወሻ: ***አስፈላጊ የሆኑት** የቡድ አባላትን ያመለክታል

**ቡድኑ በIEP ስብሰባ ላይ ምን ይወያያል?**

- የልጅዎ ጠንካራ ጎኖች እና የትምህርት ፍላጎቶች፣ እና በትምህርት ቤት እንዴት እየሰሩ እንደሆነ (በአካዳሚክ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና ባህሪ) እና የቅርብ ጊዜ ፈተናዎች ውጤቶች
- የልጅዎ አካል ጉዳተኝነት በትምህርታቸው እና በእድገታቸው ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያመጣ
- ማንኛውም የባህሪ ወይም የተግባቦት ፍላጎቶች
- እርስዎ እና ትምህርት ቤቱ ስለ ልጅዎ እድገት ለመወያየት እንዴት እየተገናኙ እንደሚቆዩ
- ልጅዎ 14 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ፣ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ የህይወት ግቦቻቸው (ኮሌጅ፣ ስራ፣ ገለልተኛ ኑሮ፣ ወዘተ.)
- ነጻ እና ተገቢ የሆነ የህዝብ ትምህርት (FAPE) ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ልጅዎ ሊያስፈልጋቸው የሚችላቸው ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች፣ እንዲሁም ሌሎች ድጋፎች እና ታሳቢዎች
- ልጅዎ በዝቅተኛ ገዳቢ የሆነ አካባቢ (LRE) መማሩን ማረጋገጥ። ይህ ማለት ልጅዎ በተቻለ መጠን እና አቅም በአብዛኞውቹ የትምህርት ቀናቶች በተለምዶ በማደግ ላይ ካሉ እኩዮች ጋር የተማሩ ነው ማለት ነው።

**በስብሰባው ላይ ምን ምን ውሳኔዎች ይደረጋሉ?**

- ልጅዎ በዓመቱ ውስጥ የትኞቹ ግቦች ላይ መስራት እንዳሉበት እና ለመማር እና ትምህርት ላይ አስፈላጊውን እድገት ለማሳየት ምን ዓይነት መስተንግዶዎች/ማሻሻያዎች እንደሚያስፈልጉዋቸው
- ልጅዎ የስቴት ወይም የትምህርት ቤት ምዘናዎችን እንዴት እንደሚወዱ እና በምን አይነት ዲፕሎማ ላይ እየሰሩ እንደሆኑ
- ትምህርት ቤቱ በልጅዎ ግቦች ላይ እድገትን እንዴት እንደሚከታተል እና እንደሚለካ—እና በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ዝማኔዎችን እንደሚያገኙ
- ልጅዎ ምን አይነት ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች፣ በምን ያህል ጊዜ፣ የት እና ለምን ያህል ጊዜ እንደሚያገኙ
- ልጅዎ 14 ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ፣ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኋላ ለህይወት ለመዘጋጀት ምን አይነት የሽግግር አገልግሎቶች ያስፈልጋሉ (ክፍሎችን፣ ስልጠናዎችን እና የማህበረሰብ ልምዶችን ጨምሮ)

## በIEP ስብሰባው ወቅት እንደ ወላጅ/አሳዳጊ ያለኝ ሚና ምንድን ነው?

- በስብሰባው ወቅት ውይይቱ ላይ ንቁ ተሳትፎ ያድርጉ። ማስታወሻ፡ ለመሳተፍ የቋንቋ ትርጉም እና/ወይም የ*ADA* መስተንግዶ ከፈለጉ ትምህርት ቤቱን ያሳውቁ።
- ሃሳቦችዎን፣ አመለካከቶችዎን እና የሚኖርዎትን ማንኛውንም ስጋት ለማካፈል አያመንቱ።
- እንደየ አስፈላጊነቱ ጥያቄዎችን እና ማብራሪያ ይጠይቁ።
- በ*IEP* ቡድን ውሳኔዎች ላይ መስማማትዎን ወይም አለመስማማትዎን ለመግለጽ ያስቡበት። *IEP*ው ተግባራዊ ለማድረግ እና/ወይም ለውጦችን ለማድረግ የእርስዎ ፈቃድ ያስፈልጋል። በመጨረሻው ረቂቅ ከተስማሙ፣ *IEP*ው እንዲተገበር ፈቃድ እንዲሰጡ ይጠየቃሉ። ፈቃድ ከመስጠትዎ በፊት *IEP*ውን መገምገም ከፈለጉ፣ የመጨረሻውን ረቂቅ ገምግመው ለተፈረመበት ትምህርት ቤት መመለስ ወይም ከስብሰባው በኋላ በኤሌክትሮኒክ መንገድ ፈርመው መላክ ይችላሉ። *(እባክዎ የጽሁፍ ፈቃድ እስኪሰጡ ድረስ፣ ትምህርት ቤቱ በአዲሱ IEP ውስጥ የተገለጹትን ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን መጀመር እንደማይችል ልብ ይበሉ።)*

## ለIEP ስብሰባው መዘጋጀት

የበለጠ ዝግጁነት እና በራስ የመተማመን ስሜት እንዲሰማዎት የሚከተሉት ነገሮችን ማድረግ ይችላሉ፦

PRC የIEP ቪዲዮ ሞጁሎች
WATCH NOW

- ☑ የIEP ሂደት ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። PRC በዓመቱ ውስጥ ስለ IEP ጠለቅ ያለ ትምህርት እሰጣል፣ እና ክፍሉን አሁን በመስመር ላይ ማየት ይችላሉ። ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም ለ IEP ስብሰባዎ ዝግጅት ላይ እገዛ ከፈለጉ PRCን በ 703.228.7239 ወይም prc@apsva.us ያግኙ።
- ☑ ልጅዎ በIEP ስብሰባው ውስጥ ስለሚኖረው ትርጉም ያለው ተሳትፎ ከልጅዎ የጉዳይ አገልግሎት አቅራቢ ጋር ይነጋገሩ።
- ☑ የልጅዎን የብቁነት ክፍሎችን፣ የቅርብ ጊዜ የሪፖርት ካርዶችን፣ የፈተና ውጤቶችን እና የቀደሙ የIEP እድገት ማስታወሻዎችን ይገምግሙ እና ያደራጁ። ከቡድኑ ጋር ለመወያየት ዝግጁ እንዲሆኑ ስለልጅዎ ጥንካሬዎች እና እርዳታ የሚያስፈልጓቸው መስኮችን ያስቡ። የልጅዎ የIEP ሂደት ማስታወሻዎች እና የሪፖርት ካርዶች በParentVue ውስጥ ይገኛሉ።
- ☑ ስለ ትምህርት ቤት ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ ከልጅዎ ጋር ያውሩ።
- ☑ ቡድኑ ግምት ውስጥ እንዲስገባ የሚፈልጉትን ሃሳቦችን እና ጥያቄዎችን የPRCን የIEP ግቤት ናሙና በመጠቀም አስቀድመው ያስገቡ። ።
- ☑ የIEP ረቂቅ ካለው የአካዳሚክ ስኬት/ተግባራዊ አፈጻጸም እና ዓመታዊ ግቦች ከIEP ስብሰባው ሁለት ቀናት ቀደም ብሎ ይገኛሉ። ረቂቁን እንዲቀበሉ ለማረጋገጥ ከልጅዎ የጉዳይ አገልግሎት አቅራቢ ጋር እቅድ ያድርጉ እና ረቂቁን ጊዜ ወስደው በጥንቃቄ ይገምግሙ። የPRC IEP ክፍል ውጤታማ እና ሊለኩ የሚችሉ ግቦችን ማዘጋጀትን ይመለከታል።
- ☑ በስብሰባው ወቅት መጠየቅ የሚፈልጉትን ጥያቄዎች ከታች “የመነጋገሪያ ነጥቦች” የሚለው ክፍል ላይ ይጻፉት።
- ☑ በስብሰባው ወቅት መጠየቅ የሚፈልጉትን ጥያቄዎች ከታች “ጥያቄዎች” የሚለው ክፍል ላይ ይጻፉት።
- ☑ አንድን ሰው (እንደ ጓደኛ፣ ጠበቃ ወይም የቤተሰብ አባል) ከእርስዎ ጋር ወደ ስብሰባው ለማምጣት ካሰቡ ቦታ እና ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት እንዲችል ትምህርት ቤትዎ አስቀድመው ያሳውቁ።

| **ሊታሰብባቸው የሚገባ ጥያቄዎች** | **የመነጋገሪያ ነጥቦች/ተጨማሪ ጥያቄዎች** |
|---|---|
| • በልጄ የ*IEP* ግቦች ላይ መረጃ ማን ይሰበስባል፣ እና እንዴት እና መቼ ነው መረጃ ከእኔ እና ከቡድናችን ጋር የሚጋራው*?*<br>• የልጄ አገልግሎቶች በሳምንት ውስጥ ምን ይመስላል*?*<br>• ለልጄ አገልግሎቶች የሚሰጠው ማን ነው*?*<br>• የልጄን የ*IEP* ግቦች ለመደገፍ በቤት ውስጥ ምን ማድረግ እችላለሁ*?*<br>• በታቀደው *IEP* ምን ያህል መስማማት አለብኝ*?*<br>• ልጄ ወደ ዓመታዊ የ*IEP* ግቦች በቂ እድገት ካላደረገ ምን ይሆናል*?*<br>• ስብሰባችንን ዛሬ ማጠናቀቅ ካልቻልን የ*IEP* ቡድናችን ምን ያደርጋል*?*<br>• በታቀደው *IEP* ወይም በ*IEP* ላይ በተደረገው ለውጥ መስማማቴን  ለመወሰን ተጨማሪ ጊዜ ብፈልግስ*?* | |

**LEARN MORE**

እርስዎ ለመርዳት PRC እዚህ ይገኛል። 703.228.7239 ላይ ይደውልሉን ወይም prc@apsva.us ኢሜል ይላኩልን።

PEATC:- ጠቃሚ የወላጅ መብቶች

የVDOE የIEP የብቁነት ቪድዮ

የPRC የIEP የቤተሰብ ግቤት ናሙና

PEATC: FAPE

PEATC: LRE

PEATC: ስኬታማ IEPዎች